ነፍጠኞች አቡበንቲ የተባለ ሽቶ አንድ ብር ይሸጡልናል። ሶስት እንቁላል ግን ከኛ በአምስት ሳንቲም ይገዛሉ። ወተትና እንጀራ መሸጥ በኦሮሞ ነውር ነው። እነሱ ግን እንጀራ መሸጥ ጀምረዋል። ይህ ነው ሥልጣኔ ? ቁንዲፍቱ መጥመቅ የኦሮሞ አይደለም። የሰው ሚስት መወሸም የኦሮሞ አይደለም። ነፍጠኖች ባህላችንን አቆሸሹት መሬታችንን ነጠቁን። መሬታችን ቅቤ ነው ። ጥቁር ቅቤ ነው መሬታችን! ያስጎመጃል! ምንሊክ የሚባለው ስግብግብ ይህን ሀብታም መሬት ሲያይ ጎመጀ። እኛን ማክበር አቃተው። እንደፈረስ ልጋልባችሁ አለን። አሻፈረን አልነው። በመሳሪያ ብዛት ተማምኖ ጨፈጨፈን። የሴቶቻችንን ጡት ጥሬ ሥጋ እንደሚበላ ሆዳም ሰው እየተስገበገቡ ቆረጡት። የሴቶቻችንን ጡት እኛ ከበግ ላይ ፀጉር እንደምንሸልተው እንዲያ ነበር የሚቆርጡት። እነዚህ ሰዎች በግ ሲያርዱ " በስም-አብ" ብለው ይጀምራሉ። የሴቶቻችንን ጡት ሲቆርጡ ግን " በስመ-አብ " አይሉም። ግን ሀይማኖት አለን ይሉናል። ታዲያ ፈጣሪ የሚያየው የትኛውን ደም ነው? ወገኖቼ ውሻ ለምን እንደተዋረደ ታውቃላችሁ? ሲረግጡት እይተረገጠ፣ ሲጨቁንት እየተጨቆነ፣ ሲያዋርዱት እየተዋረደ፣ ጭራውን ስለቆላ ነው። ውሻ ሲበድሉት ተቆጥቶ አልገዛም ብሎ ቢሆን ኖሮ የልጆቻችን ሥም ይህን ጊዜ "ውሾ" በሆነ ነበር - እና የውሻን መሰደቢያነት በህግ ብቻ መለወጥ ይቻላል!?